በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ. 218426
ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ንጉሴ ቱፋ -- ከጠበቃ ሰለሞን ሀይሉ ጋር ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ለኢትዮጵያ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤክርስቲያን -ጠበቃ ሰላማዊት ንጉሴ

2. የቦሌ ክፍለ ከተማ ይዞታ አስተዳደር ፕሮጀክት ጽ/ቤት አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 21 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 125766 ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በማጽናት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 279977 ታህሳስ 4 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ በቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አዋሳኙ በክሱ ላይ የተገለጸው ይዞታ አለኝ፤ አመልካች በስማቸው ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታው ላይ ግብር እየገበሩበት ነው፤ አመልካች እየተቃወምኩ 1ኛ ተጠሪ በይዞታዬ ላይ አጥር አጥሯል፤ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ በካርታ ቁጥር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቦሌ 10/134/2/9236354/00 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በህገወጥ መንገድ አሰርቷል፤ 2ኛ ተጠሪ ከህግ ውጪ ለ1ኛ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅቶ የሰጠው መሆኑን በመግለጽ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠው ካርታ ተሰርዞ ያጠረውን አጥር አፍርሶ ለአመልካች እንዲያስረክብ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጠው መልስም ለ1ኛ ተጠሪ በ1998 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ከ2500 ካ.ሜ ያላነሱ የእምነት ቦታ እንዲሰጠን በተሰጠው ውሣኔ መሰረት እንዲፈጸምልን በተለያየ ግዜ ጥያቄ አቅርበን ለ1ኛ ተጠሪ 2500 ካ.ሜ የአምልኮ ቦታ እንዲሰጠን ተወስኖልናል፤ ይህንን ውሳኔ ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ በቀን 15/05/2010 ዓ.ም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከንቲባ ጽ/ቤት፣ የከንቲባ ጽ/ቤትም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ቢሮ የመሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮም በእርሱ ስር ለሚገኘው ለመሬት ባንክ እና ማስተላለፍ ጽ/ቤት በአብይ ኮሚቴው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም ትዕዛዝ ሰጥቷል፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ባንክ ማስተላለፍ ጽ/ቤትም የመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ ጽ/ቤትም ወይም ኤጀንሲ በቀን 18/09/2012 ዓ.ም በተፃፈ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ስፋቱ 2008 ካ.ሜ ተዘጋጅቶ በተላከው መሰረት ከሊዝ ክፍያ ነፃ ተረክበናል፤ ለክርክር መነሻ የሆነው ቦታ ከእዳ እና እገዳ ነፃ መሆኑ ተረጋግጦ የቦታ ማስረከቢያ ቅጽ ላይ ተፈራርመን ከመሬት ባንክ ወጪ ተደርጎ በ1ኛ ተጠሪ ስም የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቶናል፤ከሚመለከተው አካል የግንባታ ፍቃድ እና ምስክር ወረቀት በተሰጠን መሰረት አጥር አጥረን ግንባታ ጀምረናል፤ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ ላይ የአምልኮ ስርዓት እየተካሄደ ይገኛል፤ አመልካች በይዞታው ላይ ከ1986-2003 ዓ.ም ግብር ገብሬአለሁ ይበሉ እንጂ የቀረበው ደረሰኝ ለየትኛው ይዞታ የተገበረበት መሆኑን የማያሳይ በመሆኑ የአመልካች ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጠው መልስም 2ኛ ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ላይ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ መስከረም 23 ቀን 1998 ዓ.ም በቃለጉባኤ የተደገፈ ነው፤ በወረዳ 10 ክልል ውስጥ 2008 ካ.ሜ መሬት ባንክ የገባ መሬት በ2012 ዓ.ም ከባንክ ወጪ ሆኖ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የሊዝ ውል በመፈራረም ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በ2ኛ ተጠሪ ተዘጋጅቶላቸዋል፤ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታው በእጃቸው አድርገው ሲጠቀሙበት አልነበረም፤ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ ለረጅም ግዜ በመንግስት ጥበቃ ስር የነበረ ይዞታ በመሆን 2ኛ ተጠሪ ከቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ባንክ እና ማስተለላፍ ጽ/ቤት በመጣለት ፕላን ፎርማት በተፈጠረላቸው መብት መሰረት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለ1ኛ ተጠሪ አዘጋጅቶ ሰጥቷል፤ 2ኛ ተጠሪ የይዞታው ባለቤት መሆኑን ማስረጃ በቀረበለት መሰረት ህግ እና መመሪያን ተከትሎ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠቱ ተጠያቂ አያደርገውም፤ ካርታ የመስጠት እና የመሰረዝ ስልጣን የአስተዳደር እንጂ የፍርድ ቤት አለመሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በተጠሪዎች የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚዎች በብይን ውድቅ ያደረገ ሲሆን በፍሬነገር ላይ ደግሞ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና የሚመለከታቸው አካላት ስለጉዳዩ አጣርተው ምላሽ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ አመልካች ያቀረበው የግብር ደረሰኝ ለአከራካሪው ይዞታ የተከፈለ ስለመሆኑ አያረጋግጥም፤ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ ለእርሻ እና ለግጦሽ ከመቼ እስከ መቼ እንደተጠቀመበት በምስክሮች አላስረዳም፤ አመልካች ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አየተጠቀመበት ስለመሆኑ አልተረጋጠም፤ 1ኛ ተጠሪ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአምልኮ ቦታ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ውሳኔ ተሰጥቷቸው ሳይፈጸምላቸው ከይገባኛል ነጻ ሆኖ በመሬት ባንክ ተይዞ የሚገኘውን አከራካሪውን ይዞታ ከእዳ እና እገዳ ነፃ መሆኑ ተረጋግጦ እንደተሰጣቸው ተረጋግጧል፤ ስለሆነም ለ1ኛ ተጠሪ ለክርክር መነሻ በሆነውን ይዞታ ላይ የተሰጠው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት የሚሰረዝበት የህግ አግባብ የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተሰርዟል፡፡

አመልካች ታህሳስ 21 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- ለክርክር መነሻ የሆነውን ይዞታ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በቁጥጥራቸው ስር አድርገው ግብር እየገበሩ ለእርሻ እና ግጦሽ እንደሚከጠቀሙበት ተረጋግጧል፤ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠው ካርታ ከመመሪያ ቁጥር 17/2006 ውጪ የተሰጠው ነው፤ ለክርክር መነሻ የሆነ መሬት ባንክ መቼ እንደገባ በምን አግባብ ይዞታው እንደተሰጠ የሚመለከተው አካል ማብራሪያ ባልሰጠበት ሁኔታ ከመሬት ባንክ ወጪ ተደርጎ እንደተሰጠ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ውድቅ የመደረጉን አግባብ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ አንጻር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

1ኛ ተጠሪ ሚያዝያ 20 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ያቀረባቸው የግብር ደረሰኞች ለየትኛው ቦታ እንደተከፈለ አያረጋግጥም፤የአመልካች ምስክሮች ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት የእሱ እንደነበረ፣ ከሆነስ ከመቼ ጀምሮ በእጁ አድርጎ ሲጠቀምበት እንደነበር አላስረዱም፤ አመልካች ይዞታው የእሱ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረቡም፤ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ መሬት ባንክ ውስጥ እንደነበረ ከሚመለከተው አካል ተረጋግጧል፤ ለክርክር መነሻ የሆነው ቦታ የከተማ ቦታ ነው፤ 1ኛ ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነውን ይዞታ ከእዳ እዳ እና እገዳ ነፃ መሆኑ ተረጋግጦ ተረክቦታል፤ ካሳ እና ምትክ ቦታ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው፤ አመልካች የጠቀሳቸው መመሪያዎች ለግራ ቀኞችን ጉዳይ አግባብነት የለውም፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በግራ ቀኙ መካከል በስር ፍ/ቤት ከተደረገው አጠቃላይ ክርክር እና ከተሰጠው ውሣኔ እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የሚያሳየው በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አዋሳኙ በክሱ ላይ የተገለጸው ይዞታ አለኝ፣ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታው ላይ ግብር እየገበርኩበት ነው፣ እየተቃወምኩ 1ኛ ተጠሪ በይዞታዬ ላይ አጥር አጥሯል፣ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ በካርታ ቁጥር ቦሌ 10/134/2/9236354/00 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በህገወጥ መንገድ አሰርቷል፣ 2ኛ ተጠሪ ከህግ ውጪ ለ1ኛ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅቶ ሰጥቷል የሚል መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ተጠሪዎች በጥቅሉ የተከራከሩት ይዞታው በህግ አግባብ በከተማው ካቢኔ ተፈቅዶ ከመሬት ባንክ ወጥቶ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ መሆኑን አንስተው ተከራክረዋል፡፡

ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው የስር ፍ/ቤት የሚያከራክረውን ነገር ለይቶ ጭብጥ በመያዝ በአግባቡ አጣርቶ የመወሰኑን አግባብነት ነው፡፡

በአንድ ክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ወገን ያመነውን ወይም አለ ብሎ የሚከራከረውንና ከክርክሩ ጋር አግባብነት ያለውን የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ጉዳይ ሌላኛው ወገን ሲክድ ፣ እንዲሁም በክሱና በመከላከያው መልስ ውስጥ የተዘረዘሩትን ነገሮች፣ ተከራካሪዎቹ ያቀረቡትን የፅሑፍ ማስረጃ፣ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 241 መሠረት በተደረገው ምርመራ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 246 እና ተከታታዬቹ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ክስ የሚያሳየው በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አዋሳኙ በክሱ ላይ የተገለጸው ይዞታ አለኝ፣ አመልካች በስማቸው ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታው ላይ ግብር እየገበሩበት ነው፣ አመልካች እየተቃወምኩ 1ኛ ተጠሪ በይዞታዬ ላይ አጥር አጥሯል፣ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ በካርታ ቁጥር 10/134/2/9236354/00 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በህገወጥ መንገድ አሰርቷል፣ 2ኛ ተጠሪ ከህግ ውጪ ለ1ኛ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅቶ የሰጠው መሆኑን የሚል ሲሆን የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከቀረበው የግራ ቀኙ ክርክር አኳያ ተገቢውን ጭብጥ መስርቶ ውሣኔ ስለመስጠቱ የውሣኔው ገጽ 7 የመጨረሻው ክፍል ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተገቢው ጭብጥ ተመስርቶ ጉዳዩ አልተመረመረም በሚል የሚያቀርቡት ክርክርም ሆነ የማስቀረቢያ ነጥቡ ተገቢነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሌላ በኩል አመልካች በስር ፍ/ቤት የቀረበው ማስረጃ በአግባቡ አልተመረመረም በሚል የሚከራከሩ ከመሆኑ አንፃር ክርክራቸውን የሚያስረዳላቸው ማስረጃ ስለማቅረብ አለማቅረባቸው በቅድሚያ በስር ፍ/ቤት ተጣርቷል ወይስ አልተጣራም የሚያሰኝ በመሆኑ ይህን ነጥብ በተመለከተ ግን አመልካች የሚያከራክረው ይዞታ የራሳቸው ስለመሆኑ እና ከመቼ እስከ መቼ ይዘውት የቆዩ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥላቸው ማስረጃ ከሣሽ እንደመሆናቸው መጠን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ይህን ነጥብ በማስረጃ ማረጋገጣቸውን የሚያሳይ ክርክር በስር ፍ/ቤት አልተመለከትንም፡፡ እንዲሁም እያከራከረ ያለው ይዞታ የከተማ ይዞታ ከመሆኑ አኳያ አመልካች ይዞታውን በምን አግባብ አግኝተው ሲጠቀሙ የነበረ መሆኑንም ሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ከይዞታ ማረጋገጫ እኩል ይዞታው የራሳቸው ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ባላቀረቡበት ግብር ስገብር ነበር በሚል የሚከራከሩ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ግን ከአመልካች በተሻለ ማስረጃ የይዞታ ማረጋገጫ በማቅረብ እና ይዞታውንም እንዴት እንዳገኘው በሚያሳይ መልኩ ያረጋገጠ መሆኑን ክርክሩ ያሳያል፡፡

በኢፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡ በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ከላይ በተገለፀው መልኩ የስር ፍ/ቤቶች ባላቸው ማስረጃን የመመዘን እና ፍሬ ነገርን የማጣራት ሥልጣናቸው በሚያከራክረው ይዞታ ላይ አመልካችን ባለቤት የሚያደርግ ማስረጃ የሌለ መሆኑን በማረጋገጥ የወሰኑ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ በማስረጃ ምዘናም ሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት ግድፈት ያላገኘ በመሆኑ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 279977 በ4/4/2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 125766 በ4/2/2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2) በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

**መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

*አ/መ*  *የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም